# ለዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 32ኛ (ሰላሳ ሁለተኛ) መደበኛ እና 28ኛ (ሃያ ስምንተኛ) አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች በኢፌዲሪ የንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣367(1)፣370፣393 እና 400፣ እንዲሁም በባንኩ መመስረቻ ፅሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ታኅሣስ 16 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በቅደም ተከተል በሚሊኒየም አዳራሽ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

| | |
|---|---|
| የአክሲዮን ማኅበሩ ስም | ዳሽን ባንክ አ.ማ. |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ዓይነት | የባንክ ሥራ ውስጥ የተሰማራ የአክሲዮን ማኅበር |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ | 14,336,972,000 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 14,336,972,000 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር | 04/2/01821/88 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ድረ-ገፅ | www.dashenbanksc.com |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ | አዲስ አበባ ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፣ የቤት ቁጥር አዲስ |

## የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የጉባዔውን አጀንዳውን ማፅደቅ
2. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የነባር አክሲዮኖችን ግዥና ዝውውሮችን ማሳወቅ
3. የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
4. የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
5. የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን መወሰን
6. በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት ፖሊሲ እና የአሠራር ሥርዓት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፤
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ክፍያና አበል መወሰን፤
9. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማፅደቅ፤

## የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. የጉባዔውን አጀንዳውን ማፅደቅ፤
2. የዳሽን ባንክ አ.ማ. የመመስረቻ ፅሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብን በማዋሃድ የተሻሻለው የመመስረቻ ፅሑፍ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፤
3. የባንኩን ካፒታል ስለማሳደግ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
4. የጉርሻ አክሲዮኖችን (Bonus Shares) በተመለከተ ተወያይቶ መወሰን፤
5. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማፅደቅ፤

## ማሳሰቢያ

- በጉባዔው ላይ በግንባር መገኘት የማይችሉ ከሆነ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፊት ለፊት በሚገኘው የዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት 14 ተኛ ፎቅ የቦርድ ፅሕፈት ቤት በመቅረብ የውክልና ቅፅ በመሙላት ከስብሰባው ከሶስት ቀን በፊት ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
- በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባዔው በአካል የምትገኙ ባለአክሲዮኖች ማንነታችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት የተረጋገጠ ሕጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትቀርቡ ተወካዮች የወካያችሁን ማንነት የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
- በዕለቱ ሁሉም ባለአክሲዮኖች የብሔራዊ (የፋይዳ) መታወቂያችሁን እንዲሁም የግብር መክፈያ መለያ ቁጥራችሁን (Tax Identification Number) ይዛችሁ በስብሰባው እንድትገኙ እናሳስባለን፡፡
- ባለአክሲዮኖች በሥራ ላይ ያሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉና ድምጽ እንዲሰጡ መወከል አይችሉም፡፡
- የመመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻያን እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት ፖሊሲ እና የአሠራር ሥርዓትን በተመለከተ የተዘጋጀውን ሠነድ ከባንኩ ድረ-ገፅ (www.dashenbanksc.com) ላይ ወይም በዳሽን ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት 14ተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው የቦርድ ፅሕፈት ቤት በአካል በመቅረብ ማግኘት ይቻላል፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ
ዳሽን ባንክ አ.ማ.